የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ መጋቢት ፲፱ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 31
ADDIS ABABA 28th March 2014


ማውጫ


ደንብ ቁጥር ፫፻፭/፳፻፮ ዓ.ም

የቅጅና ተዛማጅ መብቶች የሚያስገኙ ሥራዎች ምዝገባ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ....................ገፅ ፯ሺ፫፻፸፭
ሠንጠረዥ..........................................ገፅ ፯ሺ፫፻፹፩


CONTENTS


Regulation No. 305/2014

Registration of Works Entitling Copyright and Neighboring Rights Council of Ministers
Regulation.................................................. Page 7375
Schedule ..................................................... Page 7381


## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፭/፳፻፮

## የቅጅና ተዛማጅ መብቶች የሚያስገኙ ሥራዎች ለመመዝገብ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፳፻፫ አንቀጽ ፭ እና በቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር ፬፻፲/፲፱፻፺፮ አንቀጽ ፴፱(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የቅጅና ተዛማጅ መብቶች የሚያስገኙ ሥራዎች ምዝገባ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፭/፳፻፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

፩/ "አዋጅ" ማለት የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር ፬፻፲/፲፱፻፺፮ ነው፤

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ፤

፫/ "ጽሕፈት ቤት" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፫፻፳/፲፱፻፺፭ የተቋቋመው የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ነው፤

፬/ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል፡፡


ያንዱ ዋጋ
Unit price 5.25


## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 305/2014

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE REGISTRATION OF WORKS ENTITLING COPYRIGHT AND NEIGHBORING RIGHTS

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 39(1) of the Copyright and Neighboring Rights Protection Proclamation No. 410/2004.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Registration of Works Entitling Copyright and Neighboring Rights Council of Ministers Regulation No. 305/2014".

### 2. Definitions

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "Proclamation" means the Copy Right and Neighboring Rights Protection Proclamation No. 410/2004;

2/ definitions provided for under Article 2 of the Proclamation shall be applicable to this Regulation;

3/ "Office" means the Ethiopian Intellectual Property Office established by Proclamation No. 320/2003;

4/ any expression in the masculine gender includes the feminine.


ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

**፫. ስለምዝገባ**

፩/ የቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኙ ሥራዎች ባለቤት ወይም መብቱ የተላለፈለት ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ መሠረት ለጽሕፈት ቤቱ በማመልከት መብቱን ማስመዝገብ ይችላል፡፡

፪/ ጽሕፈት ቤቱ የቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኙ ሥራዎችን በዚህ ደንብ መሠረት የመመዝገብና የናሙና ስራዎችን ጠብቆ የማቆየት ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

**፬. የቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኙ ሥራዎች ምድብ**

የቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኙ ሥራዎች በሚከተሉት ምድብ መሠረት ሊመዘገቡ ይችላሉ፡-

፩/ የፅሁፍ ወይም የቃል ሥራ፤

፪/ የመድረክ፣ የሙዚቃና የኦዲዮቪዥዋልና የመሳሰሉት የኪነ-ጥበብ ሥራዎች፤

፫/ የፎቶግራፍ፣ የሥዕል፣ የግራፊክስና የኪነ-ሕንፃን የመሳሰሉ የሥነ-ጥበብ ሥራዎች፤

፬/ የኮምፒውተር ፕሮግራሞች፤

፭/ የድምፅ ሪከርድ፤

፮/ ብሮድካስት፡፡

**፭. የምዝገባ መመዘኛዎች**

ቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኝ ማንኛውም ሥራ ሊመዘገብ የሚችለው በአዋጁ አንቀጽ ፮ ላይ የተመለከቱትን መመዘኛዎች ሲያሟላ ይሆናል፡፡

**፮. ስለምዝገባ ማመልከቻ ይዘት**

፩/ የቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኝ ሥራ ለማስ መዝገብ ለጽሕፈት ቤቱ የሚቀርብ ማንኛውም ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡-

ሀ) የአመልካቹ ሙሉ ስም፣ አድራሻና ዜግነት፤

ለ) አመልካቹ በሥራው ላይ ያለው የጥቅም ዓይነት፤

ሐ) የሥራው ምደባና መግለጫ፤

መ) የሥራው ርዕስ፤

ሠ) ሥራው የተዘገጀበት ቋንቋ፤

ረ) የሥራው አመንጪ ስም፣ አድራሻና ዜግነት፤

ሰ) የሥራው አመንጪ በሕይወት የሌለ እንደሆነ የሞተበት ቀን፤

ሸ) ሥራው የታተመ መሆን አለመሆኑ፤

**3. Registration**

1/ The owner of copy right or neighboring right or any person to whom such right is assigned may register his right by applying to the Office in accordance with this Regulation.

2/ The Office shall have the responsibility to register works entitling copyright and neighboring rights in accordance with this Regulation and, preserve sample works.

**4. Classification of Works Entitling Copyright and Neighboring Rights**

Works entitling copyright and neighboring rights may be registered in accordance with the following classifications:

1/ literary or oral works;

2/ artistic works such as stage, music and audio visual works;

3/ visual arts such as photographs, drawings, graphics and works of architecture;

4/ computer programs;

5/ sound recordings;

6/ broadcast.

**5. Requirements for Registration**

Any work entitling copyright and neighboring rights may be registered upon fulfilling the requirements provided for under Article 6 of the Proclamation.

**6. Content of Application for Registration**

1/ Any application to be submitted to the Office for registration of copyright and neighboring rights shall contain the following particulars:

a) the full name, address and nationality of the applicant;

b) nature of the applicant's interest in the work;

c) class and description of the work;

d) title of the work;

e) language of the work;

f) name, address and nationality of the author;

g) if the author is deceased, the date of his decease;

h) whether the work is published or unpublished;

ቀ) ሥራው የታተመ ከሆነ መጀመሪያ የታተመበት ዓመት፣ የታተመበት አገር እና የአሳታሚውስም፣አድራሻና ዜግነት፤

በ) ሥራው በተከታታይ የታተመ ከሆነ የታተመባቸው ዓመታት፣ የታተመባቸው አገሮች እና የአሳታሚዎቹ ስም፣ አድራሻና ዜግነት፤

ተ) ጽሕፈት ቤቱ በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች መረጃዎች፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከሥራው ናሙና እና ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡-

ሀ) የአመልካቹ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ኮፒ፤

ለ) አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ ሕጋዊ ሰውነት ማግኘቱን የሚያሳይ ሰነድ፤

ሐ) እንደ አስፈላጊነቱ የውክልና ማስረጃ፤

መ) አመልካቹ የሥራው አመንጪ ካልሆነ ባለመብትነት ያገኘበት ሰነድ፤

ሠ) በዚህ ደንብ መሠረት የተፈጸመ የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ፤

ረ) ጽሕፈት ቤቱ በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች ሰነዶች፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ከማመልከቻ ጋር ተያይዞ የሚቀርብ ማንኛውም ሰነድ በአማርኛ ወይም በእንግሊዘኛ የተዘጋጀ ካልሆነ የአማርኛ ወይም የእንግሊዘኛ ትርጉሙ አብሮ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

፯. **የምዝገባ ማመልከቻ አቀራረብ**

፩/ ማንኛውም የቅጅና ተዛማጅ መብት ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻ በአማርኛ ወይም በእንግሊዘኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

፪/ ማመልከቻውና ተያያዥ ሰነዶች በጽሕፈት ቤቱ የፖስታ ወይም የድረ-ገጽ አድራሻ ሊላኩ ይችላሉ፡፡

፫/ ማመልከቻው በፖስታ ቤት በኩል የሚላክ ሲሆን የጽሕፈት ቤቱን ትክክለኛ ስምና አድራሻ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም ጽሕፈት ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አመልካቹ ወይም ወኪሉ በግንባር እንዲቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

i) year and country of first publication and name, address and nationality of the publisher if the work is published ;

j) years and countries of subsequent publications, if any, and names, addresses and nationalities of the publishers;

k) other information as determined by directive of the Office.

2/ Any application to be submitted pursuant to sub-article (1) of this Article shall be accompanied with sample of the work and the following documents:

a) copy of the identity card or passport of the applicant;

b) if the applicant is a legal person, document showing the acquisition of its legal personality;

c) power of attorney as may be necessary;

d) if the applicant is not the author, document showing that he is a right holder;

e) receipt of payment of service fee effected in accordance with this Regulation;

f) other documents as determined by directive of the Office.

3/ If Any document attached to an application to be submitted pursuant to sub-article (2) of this Article is not executed in the Amharic or English language, it shall be translated into Amharic or English.

7. **Submission of Application**

1/ Any application for registration of copyright and neighboring rights shall be submitted in the Amharic or English language.

2/ The application and attached documents may be sent to the Office through its postal or website address.

3/ An application sent through postal service shall clearly state the name and address of the Office.

4/ Notwithstanding the provisions of sub-article (2) of this Article, the Office may, if it finds necessary, request the applicant or his agent to appear in person.

## ፰. አንድ ማመልከቻ ለአንድ ሥራ ብቻ ስለመሆኑ

፩/ ማንኛውም በዚህ ደንብ መሠረት ለጽሕፈት ቤቱ የሚቀርብ አንድ ማመልከቻ አንድ ቅጅን ወይም ተዛማጅ መብትን የሚያስገኝ ሥራን ብቻ ለማስመዝገብ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም እንደ ኢንሳይክሎፒዲያ ያሉ በተከታታይ ክፍሎች የታተሙ ሥራዎች አንድ ማመልከቻ ብቻ በማቅረብ ሊመዘገቡ ይችላሉ፡፡

## ፱. የፎርማሊቲ ምርመራ

፩/ ጽሕፈት ቤቱ የቀረበለትን ማመልከቻ ተቀብሎ በአዋጁና በዚህ ደንብ የተቀመጡት መመዘኛዎች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ የፎርማሊቲ ምርመራ ያካሂዳል፡፡

፪/ ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለፎርማሊቲ ምርመራ የቀረበለት ማመልከቻ ጉድለት ያለበት ሆኖ ካገኘው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እርማት እንዲደረግ ለአመልካቹ ወይም ለወኪሉ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

፫/ አመልካቹ ወይም ወኪሉ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን እርማት ወይም ማስተካከያ ካላደረገ ማመልከቻው እንደተተወ ይቆጠራል፡፡

## ፲. የአመልካች ቃለ መሃላ

፩/ ጽሕፈት ቤቱ በሚቀርብለት የቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኝ ሥራ ምዝገባ ማመልከቻ ላይ የባለቤትነት ማረጋገጫ የሥረ-ነገር ምርመራ አያደርግም፤ ሆኖም አመልካቹ ባለቤት ስለመሆኑ በቃለ መሃላ እንዲያረጋግጥ ይደረጋል፡፡

፪/ አመልካቹ የሰጠው ቃለ መሃላ ትክክለኛ ሆኖ ባይገኝ ለፈጸመው የማጭበርበር ተግባር አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ፲፩. የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት

ማመልከቻው የፎርማሊቲ መመዘኛዎችን የሚያሟላ ሲሆን ጽሕፈት ቤቱ ቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኝ ሥራውን በመመዝገብ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

## ፲፪. የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይዘት እና የሕግ ውጤት

፩/ ጽሕፈት ቤቱ የሚሰጠው የቅጂ እና ተዛማጅ መብት የሚያስገኝ ሥራ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፡-

ሀ) የምዝገባ ቁጥር ፣

ለ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ (፩) ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (መ) የተመለከቱትን ዝርዝሮች ፣

## 8. Unity of Application

1/ Any one application for registration to be submitted to the Office in accordance with this Regulation shall contain only one work entitling copyright or neighboring rights.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, series publication works such as encyclopedia may be registered upon submission of only one application.

## 9. Formality Examination

1/ The Office shall undertake formality examination on the application submitted to it to verify whether the requirements specified in the Proclamation and in this Regulation are fulfilled.

2/ Where the Office finds defect on the application submitted to it pursuant to sub-article (1) of this Article, it shall give a written notice to the applicant or his agent to make correction within one month.

3/ If the applicant or his agent fails to make correction within one month, the application shall be considered as abandoned.

## 10. Affidavit of the Applicant

1/ The Office may not undertake substantive examination on the application for registration to proof ownership of the work entitling copyright and neighboring rights; provided, however, that the applicant shall ascertain through affidavit that he is the owner.

2/ The applicant shall be criminally liable on the basis of relevant law for a fraud committed if the affidavit given is untrue.

## 11. Issuance of Certificate of Registration

The Office shall register a work entitling copyright and neighboring rights and issue certificate of registration if the application fulfils the formality requirements.

## 12. Contents and Legal Effect of Certificate of Registration

1/ A certificate of registration of work entitling copyright and neighboring rights issued by the Office shall contain:

a) the registration number;

b) the particulars specified from paragraphs (a) to (d) of Article 6 (1) of this Regulation;

ሐ) የማመልከቻውን ቀን፤

መ) የምዝገባውን ቀንና ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፤

የሚይዝ ይሆናል፡፡

፪/ ጽሕፈት ቤቱ የሚሰጠው የቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኝ ሥራ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ቀዳሚ የባለቤትነት ማስረጃ በመሆን ያገለግላል፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም የቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኝ ሥራ በዚህ ደንብ መሠረት አለመመዝገቡ በአዋጁ መሠረት የሚደረግ የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃን አያስቀርም፡፡

፫. የምዝገባ ምስክር ወረቀት ጸንቶ ስለሚቆይበት ጊዜና ስለእድሳት

፩/ የቅጂና ተዛማጅ መብት የሚያስገኝ ሥራ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ጸንቶ የሚቆየው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለአምስት ዓመታት ይሆናል፡፡

፪/ ባለመብቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የምዝገባ የምስክር ወረቀት ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንደተጠናቀቀ ቀጥሎ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ሊያሳድስ ይችላል፡፡

፫/ ባለመብቱ በአዋጁ የተደነገገው የመብት ጥበቃ ጊዜ ጸንቶ የሚቆይበት ዓመት እስኪያበቃ ድረስ በየአምስት ዓመቱ በተከታታይ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ሊያሳድስ ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ባለመብቱ አስፈላጊውን ክፍያ በመፈጸም የዕድሳት ጥያቄ ለጽሕፈት ቤቱ ካላመለከተ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱ ይሰረዛል፡፡

፬. ስለ መብት መተላለፍ ምዝገባ

፩/ የተመዘገበ የቅጅና ተዛማጅ መብት የሚያስገኝ ሥራ መብት ለሌላ ሰው ሲተላለፍ መብቱ የተላለፈለት ሰው መብቱ መተላለፉን የሚገልጹ አግባብ ያላቸው ማስረጃዎችን በማያያዝ ለጽሕፈት ቤቱ ማመልከቻ ማቅረብና ማስመዝገብ ይችላል፡፡

፪/ መብቱ የተላለፈለት ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከሚቀርብ ማመልከቻ ጋር የአገልግሎት ክፍያ መፈጸሙን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

c) date of the application; and

d) date and validity period of the registration.

2/ The certificate of registration of work entitling copyright and neighboring rights issued by the Office shall serve as a *prima facie* evidence of ownership of same.

3/ Notwithstanding the provisions of sub-article (2) of this Article, failure to register any work entitling copyright and neighboring rights pursuant to this Regulation may not affect the protection of copyright and neighboring rights under the Proclamation.

13. **Validity Period and Renewal of Certificate of Registration**

1/ The certificate of registration of a work entitling copyright and neighboring rights shall be valid for five years from the date of its issuance.

2/ The right holder may renew certificate of registration within six months from the date of expiry of the validity period provided under sub-article (1) of this Article.

3/ The right holder may renew his certificate of registration for five successive years until the protection years provided in the Proclamation expires.

4/ If the right holder fails to apply, upon payment of fee, to the Office for renewal of the certificate of registration within the renewal period provided under sub-article (2) of this Article, the certificate of registration shall be cancelled.

14. **Registration of Assignment of Rights**

1/ Where a registered work entitling copy right and neighboring rights is assigned, the assignee may submit an application to the Office accompanied with relevant evidences of the assignment and register his rights.

2/ The assignee shall attach evidence of payment of service fees to his application submitted in accordance with sub-article (1) of this Article.

፫/ ጽሕፈት ቤቱ የመብቱን መተላለፍ መዝግቦ መብቱ በተላለፈለት ሰው ስም የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

**፲፭. የተመዘገቡ ሥራዎች መረጃ ስለመመልከት**

፩/ ፍርድ ቤቶች፣ የፖሊስና የዐቃቤ ሕግ ተቋማት እና ሌሎች የመንግሥት ተቋማት ጽሕፈት ቤቱን በጽሁፍ በመጠየቅ የተመዘገቡ የቅጅና ተዛማጅ መብት ሥራዎችን በሚመለከት በጽሕፈት ቤቱ የተያዙ መረጃዎችን ያለክፍያ ሊመለከቱ ይችላሉ፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው ለጽሕፈት ቤቱ ማመልከቻ በማቅረብና አግባብ ያለውን ክፍያ በመፈጸም የተመዘገቡ የቅጅና ተዛማጅ መብት ሥራዎችን በሚመለከት በጽሕፈት ቤቱ የተያዙ መረጃዎችን ሊመለከት ይችላል፡፡

**፲፮. የአገልግሎት ክፍያዎች**

ጽሕፈት ቤቱ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚፈጸመው ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

**፲፯. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መጋቢት ፲፱ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

3/ The Office shall register the assignment of rights and issue certificate of registration in the name of the assignee.

**15. Access to Information of Registered Works**

1/ Courts, police and public prosecutor institutions and other public institutions may have access to information of registered works entitling copyright and neighboring rights free of charge by requesting the Office through written communication.

2/ Any person may have access to information of registered works entitling copyright and neighboring rights by applying to the Office and upon payment of the prescribed fee.

**16. Service Fees**

The service fees to be charged by the Office shall be as prescribed by Schedule attached to this Regulation.

**17. Effective Date**

Thus Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 28th day of March, 2014.

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

## የአገልግሎት ክፍያ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የአገልግሎቱ ዓይነት | የክፍያው መጠን በብር | |
|---|---|---|---|
| | | ለግለሰብ | ለድርጅ |
| ፩ | ለምዝገባ ጥያቄ ማመልከቻ | ፪፻፶ | ፫፻፲፭ |
| ፪ | ለምዝገባ ማመልከቻ እርማት | ፪፻፶ | ፫፻፲፭ |
| ፫ | የምዝገባ ዕድሳት | ፪፻፶ | ፫፻፲፭ |
| ፬ | የመብት መተላለፍ ምዝገባ | ፫፻ | ፫፻፸፭ |
| ፭ | የተመዘገቡ ሥራዎችን መረጃ ለመመልከት | ፩፻ | ፩፻፳፭ |

## SCHEDULE OF SERVICE FEES

| No. | Types of Service | Amount of Fees in Birr | |
|---|---|---|---|
| | | **Individual** | **Firm** |
| 1 | Application for Registration | 250 | 315 |
| 2 | Correction of Application | 250 | 315 |
| 3 | Renewal of Registration | 250 | 315 |
| 4 | Registration of Assignment of Rights | 300 | 375 |
| 5 | Access to Information of Registered Rorks | 100 | 125 |